የመርሃ ግብር መመሪያ (ፖሊሲ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY

**ተዛማጅ መመሪያዎች/ደንቦች፡-** ACA, ACF-RA, GCC-RA, IGP-RA, JFA, JFA-RA, JGA-RB, JGA-RC, JHC, JHC-RA, JHF, JHF-RA

**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** Chief of Districtwide Services and Supports; Human Resources and Development

# የተማሪዎች ወሲባዊ ትንኮሳ እና ወሲባዊ ጥቃት

A. **ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ መጥፎ ወሲባዊ ሥነ ምግባርን እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከልከል።

የ MCPS ሰራተኞች እና ተማሪዎች ወሲባዊ ጥሰቶችን እና ወሲባዊ ትንኮሳዎችን እንዲያውቁ፣ እንዲረዱ እና ሪፖርት እንዲያደርጉ ለመርዳት የተነደፉ የትምህርት መርሃ ግብሮች እንዲዘጋጁ ኃላፊነት ለመስጠት።

ተቀባይነት የሌለው ወሲባዊ ብልግና እና የወሲብ ትንኮሳ ቅሬታዎችን ለመፍታት ውጤታማ የአሠራር ሥርዓቶችን ማዕቀፍ ለማብጀት።

B. **ጉዳዩ**

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በማንኛውም ሁኔታ በትምህርት ፕሮግራሞቹ እና በእንቅስቃሴዎቹ፣ ወይም በንብረቱ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ማንኛውንም ዓይነት ወሲባዊ በደል ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ አይታገስም። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማዎች፣ የ MCPS ንብረት ማለት ማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም መሬትን ጨምሮ ሌሎች በ MCPS ይዞታ የሚገኙ መገልገያዎች (ፋሲሊቲዎች)፣ የ MCPS አውቶቡሶች እና ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች እና በ MCPS የሚደገፍ-ስፖንሰር የተደረገ ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴና ቦታዎችን ጭምር የሚያጠቃልል ሲሆን፥ በ MCPS ሃላፊነት ሥር የሚገኙ ግለሰቦች የተሳተፉባቸው ክስተቶች እና ተከስቷል ተብሎ የሚጠረጠር የትንኮሳ ሁኔታ ማለት ነው።

2. ተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ሶስተኛ ወገኖች ከወሲባዊ ትንኮሳ ነፃ የመሆን መብት አላቸው። ቦርዱ ሁሉም ሰዎች ከሁሉም ዓይነት ወሲባዊ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ነፃ የሚሆኑበትን የትምህርት አውድ ለመፍጠርና ለመጠበቅ እና ይህንን ፖሊሲ የሚጥሱ ባህሪያትን ለመከላከል፣ ለማረም እና የዲስፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ ነው።

3. ትርጓሜዎች

a) ጾታዊ ግብረገብን ወይም ህግን የጣሰ ተግባር

(1) ጾታዊ የስነምግባር ብልሹነት መገለጫው፡- በግለሰብ ላይ ወይም በአንድ የተወሰነ ቡድን ላይ ያተኮረ የቃል፣ የጽሑፍ ወይም አካላዊ የጾታ ትንኮሣ/ጥቃት የማድረስ ባህሪን ያጠቃልላል፣ ምክንያቱም በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ጾታ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የጾታ ማንነት፣ የሥርዓተ-ፆታ መግለጫ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የእርግዝና/የወላጅነት ሁኔታ፣ እና/ወይም በጾታ ላይ የተመሠረተ የወንድነት ወይም የሴትነት ጽንሰ-ሀሳቦችን መሠረት በማድረግ፣ ድርጊቱ ተቀባይነት የሌለው እና የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ ከሆነ፡-

(a) ለሥነ ምግባር መገዛት ወይም አለመቀበል የሚገለጸው በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ በግለሰብ ትምህርት ወይም በቃል በሚገለጽ ሁኔታ፣ ወይም በ MCPS እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ፣ ወይም

(b) ለሥነ ምግባር መገዛት ወይም አለመቀበል የግለሰቡን ትምህርት በሚነኩ ውሳኔዎች ወይም በ MCPS እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ እንደ መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ፣ ወይም

(c) የስነምግባሩ ውጤት ለግለሰቡ(ቧ) ትምህርት የሚያስፈራ/በስጋት ላይ የሚጥል፣ ጠላትነትን ወይም አስፀያፊ አካባቢ የመፍጠር ዓላማ ካለው፣ ወይም በ MCPS እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ መሰናክል የመፍጠር ሃሳብ ካለው፤ ወይም

(d) ምግባሩ በግለሰብ ትምህርት፣ ወይም በ MCPS እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም ውስጥ የመሳተፍ ችሎታን ያለአግባብ ያስተጓጉለ እንደሆን፤ እና

(2) ምግባሩ የግለሰቡ(ቧ)ን የትምህርት ጊዜ፣ ስምምነቶችና ውሎችን፣ ሁኔታዎች ወይም መብቶችን የሚያደናቅፍ፣ ወይም በ MCPS እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም ውስጥ ተሳትፎን በሚቀይር ሁኔታ ከባድ ወይም የተስፋፋ ከሆነ።

(3) ሥነ ምግባሩ በቃላት ወይም በንግግር፣ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ሊሆን ይችላል።

b) ወሲባዊ ጥቃት

(1) እንደ ወሲባዊ ትንኮሳ የሚቆጠር ምግባር በ1972 የትምህርት ማሻሻያዎች ርዕስ IX እና በአፈጻጸም ደንቦቹ እንዲሁም ክፍል (ርዕስ IX) 42 U.S.C. Section 1983 ጨምሮ በዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት እንደተተረጎመው የ MCPS ተማሪ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ካጋጠመው/ካጋጠማት በሌሎች የሲቪል መብቶችና ሕጎች መሠረት ሊተገበር ይችላል።

(a) የ MCPS ሰራተኛን ባልተፈለገ የግለሰብ ግብረ-ሥጋ ግንኙነት እንዲሳተፍ-እንድትሳተፍ ያመቻቸ(ቹ)፥ የረዳ(ች) የ MCPS ሠራተኛ፣ ተጠቃሚ ወይም አገልግሎት ሰጪ፣ ወይም

(b) አንድ ሰው የ MCPS ትምህርታዊ መርሃ ግብሮችን ወይም እንቅስቃሴዎችን በእኩልነት እንዳያገኝ-እንዳታገኝ የሚከለክል/የምትከለክል፣ በሆነ ሰው አማካይነት በጣም ከባድ፣ የተበከለ እና ተጨባጭ አፀያፊ የሆነ ተቀባይነት የሌለው ምግባር መፈጸም፤ ወይም

(c) በፌዴራል ሕግ እንደተገለጸው "ጾታዊ ጥቃት"፥ "የፍቅር ጓደኛን ማጥቃት"፥ "የቤት ውስጥ ጥቃት" ወይም "እያሸመቁ-እያደቡ ማሳደድ"።

(2) ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፥ ድርጊቱ የተፈጸመው ከዚህ በታች እንደተገለጸው ከሆነ እንደተከለከለ ወሲባዊ ትንኮሳ አይመለከትም፡--

(a) ከአሜሪካ ውጭ፣ ወይም

(b) ወሲባዊ ጥቃትና ትንኮሳው የተከሰተበት አውድ ከ MCPS ቁጥጥር ውጭ በሆነ(ኑ) ግለሰብ፥ ሁኔታና አካባቢ ከሆነ።

(3) በርዕስ IX መሠረት ምግባሩ "ወሲባዊ ትንኮሳ ነው" የሚያስብል እንደሆነ በሁኔታዎች አጠቃላይ ሁኔታ ይገመገማል፣ ይህም የባህሪውን ድግግሞሽ፣ የድርጊቱን ክብደት፣ ለአካላዊ ጉዳት አስጊነቱ ወይም ያስከተለውን ኃፍረትና ውርደት፣ ወይም አስጸያፊ ባህሪን ወይም ንግግርን ያጠቃልላል። እነዚህ ምክንያቶች በግላዊ እና በተጨባጭ እይታዎች፣ ምግባሩ በእውነቱ በሰው ላይ ያሳደረውን ተፅእኖ ብቻ ሳይሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በሆነ ሰው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅእኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ይገመገማሉ።

(4) በፌዴራል ሕግ በተገለጸው መሠረት በዝርዝር የተገለጸ የወሲብ ትንኮሳ ተግባርን የማያሟላ ምግባር በቦርድ ፖሊሲ JHF፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት መሠረት ምርመራ እና ተግሣጽ የሚያሰጥ ወሲባዊ ጥቃት ሊሆን ይችላል። በ MCPS የተማሪ የስነምግባር ኮድ፣ እና የ MCPS የሰራተኛ ስነምግባር ኮድ ።

c) እንደ ወሲባዊ በደል ወይም የወሲብ ትንኮሳ ሊቆጠር የሚችል ሥነ ምግባር፡- አፀያፊ ቀልዶችን፣ ስድቦችን፣ ምሳሌዎችን ወይም የስም አጠራርን፣ አካላዊ ጥቃቶችን ወይም ማስፈራሪያዎችን፣ ማሾፍን ወይም ስድቦችን ወይም ማዋረድን፣ አስጸያፊ ነገሮችን ወይም ስዕሎችን ሊያካትት ይችላል።

d) ሶስተኛ ወገን ማለት የ MCPS ሠራተና ወይም ተማሪ ያልሆነ(ች)/ያልሆኑ ነገር ግን በ MCPS እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፍ ወይም በ MCPS ንብረት ላይ የሚገኝ እና በ MCPS ስልጣን ወይም ቁጥጥር የሚሠራ ወይም የሚገኝ ሰውን ሊያካትት የሚችል ሲሆን፥ ነገር ግን በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በትምህርት አስጠኚዎች ብቻ የተገደበ ሳይሆን ከ MCPS ሠራተኛ ወይም ተማሪ በስተቀር ማንኛውም ሰው ሲሆን በ MCPS የሚሣተፉ በጎ ፈቃደኞች፣ የሥራ ተቋራጮች፣ ኮንትራክተሮች፣ አሰልጣኞች እና ሌሎች ሰራተኞች እና/ወይም ተማሪዎች የሚገኙበት ማለት ነው።

C. **አቋም**

1. የፖሊሲው ጥሰቶች የስቴት ወይም የፌዴራል ሲቪል እና/ወይም የወንጀል ሕጎችን የሚጥሱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ይህ ፖሊሲ የሚመለከተው እያንዳንዱ ሰው የወንጀል ቅጣቶችን የሚያስከትል መሆኑን ስለ ድንጋጌዎቹ በማሳወቅ ረገድ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ-እንድታደርግ ታዘዋል።

2. ይህ ፖሊሲ ለሁሉም የ MCPS ተማሪ ወሲባዊ ትንኮሳ ክስተቶች ተፈጻሚ ይሆናል። በተማሪዎች፣ በሠራተኞች ወይም በሦስተኛ ወገኖች የተፈጸሙ ክስተቶችንም ይመለከታል።

3. በማንኛውም ሰው ላይ አንድ ጊዜ ወይም በተደጋጋሚ ክስተቶች ወሲባዊ ትንኮሳ ሊከሰት ይችላል።

4. የሪፖርት እና ድጋፍ እርምጃዎች

    a) ተማሪዎች፣ ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው፣ የተማሪን ጾታዊ አፀያፊ ስነምግባር ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ ሲያጋጥም ወይም ሲመለከቱ የሪፖርት ምርመራው ሂደት ለሚመለከተው/ለሚመለከታት እና ሌሎች የድጋፍ እርምጃዎችን የመውሰድ ሃላፊነት ለሚመለከተው የ MCPS ሠራተኛ ጉዳዩን ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። እንዲሁም በ "Title IX sexual harassment reporting email drop box" ወሲባዊ ትንኮሳን ሪፖርት ማድረጊያ የኢሜል አድራሻ TitleIX@mcpsmd.org ላይ ሪፖርት ሊደረግ ይችላል።

    b) ስለ ወሲባዊ መጥፎ ስነምግባር ወይም በወሲባዊ ትንኮሳ ጉዳዮች ሊገኙ የሚችሉ የድጋፍ እርምጃዎችን ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁ ይደረጋል። የድጋፍ እርምጃዎች የምክር አገልግሎት፣ የግዜ ገደቦችን ማራዘም ወይም ሌላ ከኮርስ ጋር የተዛመዱ ማስተካከያዎች፣ የትምህርት ክፍል መርሃ ግብሮችን ማሻሻል፣ ወይም ችግሩ በተፈጠረባቸው ወገኖች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ገደቦችን ማድረግ የመሳሰሉትን ያካትታል፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

    c) ወሲባዊ በደል ወይም የወሲብ ትንኮሳን በቃል ወይም በጽሑፍ ሪፖርት በሚያደርግ ሰው ላይ ወይም በምርመራ ተካፋይ ወይም ተባባሪ በሆነ ግለሰብ ላይ የበቀል እርምጃን መውሰድ ቦርዱ ይከለክላል።

5. ምርመራዎች

    በተማሪዎች፣ በ MCPS ሠራተኞች፣ በኮንትራክተሮች፣ በሥራ ተቋራጮች፣ ወይም በበጎ ፈቃደኞች በተማሪዎች ላይ የተፈጸሙ ወሲባዊ ጥሰቶች ወይም የወሲብ ትንኮሳዎች በሙሉ ከርእሰ መምህሩ ወይም ተወካዩ ከተማሪዎች ደህንነት እና ስርአት አስከባሪዎች ጋር በመተባበር በስቴትና በፌዴራል ሕጎች መስፈርቶች መሠረት ምርመራ ይደረግባቸዋል።

D. **ተፈላጊ ውጤቶች**

1. ሁሉም የ MCPS ሰራተኞች እና ተማሪዎች ወሲባዊ ጥሰትን ወይም የወሲብ ትንኮሳን ሊያስከትሉ በሚችሉ በሁሉም መልኩ ተገቢ ያልሆነ ወሲባዊ ባህሪን እንዲያውቁ ግንዛቤ ተሰጥቷቸዋል።

2. ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ወሲባዊ በደል ወይም የወሲብ ትንኮሳን ሪፖርት እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸዋል።

3. ሪፖርት ስለማድረግ፣ ስለ ምርመራ፣ ምላሽ ስለመስጠት እና የድጋፍ እርምጃዎችን ስለመውሰድ ውጤታማ እና ሕጋዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

4. የ MCPS ተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ሶስተኛ ወገኖች ከወሲባዊ ትንኮሳ ነፃ በሆነ አካባቢ ይማራሉ፥ ይሠራሉ።

**E. የአፈጻጸም ስልቶች**

1. የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ፦

   a) የዚህን ፖሊሲ አፈፃፀም እና ተዛማጅ የፌዴራል እና የስቴት ህጎችን እና ደንቦችን ለማስተባበር Title IX አስተባባሪ መሾም፤

   b) በ Title IX ድንጋጌ መሠረት ለሚቀርቡት ቅሬታዎች የምርመራ ሂደቶችን ጨምሮ አፋጣኝ እና ፍትሃዊ መፍትሄ ለመስጠትና እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍ እርምጃዎችን ለመውሰድ Title IX ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም መልኩ ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር ደንቦችን ማዘጋጀት፤

   c) ወሲባዊ ጥሰትን ወይም ወሲባዊ ትንኮሳን የሚከለክሉ ይህንን ፖሊሲ እና ተዛማጅ የፌዴራል እና የስቴት ህጎችን ለተማሪዎች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማስተማር፥ እንዲሁም እንደ ማስታወቂያዎች፣ በራሪ አጫጭር ጽሑፎች፥ የማመልከቻ ቅጾች፣ ኮንትራቶች እና ሌሎች ግንኙነቶችን የሚዘረዝሩ መረጃዎችን በሰፊው በማሰራጨት ተማሪ እንዴት አቤቱታ ማቅረብ ወይም እርዳታ ማግኘት እንደምትችል-እንደሚችል ማስተማር፤

   d) ለ MCPS ሠራተኞች ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችልና የሚደግፍ ሙያዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤

      (1) የዚህን ፖሊሲ ተገቢ አፈፃፀም ለማረጋገጥ ለሁሉም ሠራተኞች ዓመታዊ የግዴታ ሥልጠና መስጠት፥ እና

      (2) ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች እና ለሌሎች በ MCPS ንብረት ላይ ተገቢ የሆነ የሥነ ምግባር ደንብ እና ሌሎች መመሪያዎችን የሚመለከት ኃላፊነት የተሞላበት ባህሪ እና ተገቢ የሥነ ምግባር ደረጃዎችን በግልፅ ማስቀመጥ፥ እና

   e) የሜሪላንድ ሕግ በሚጠይቀው መሠረት ለሁሉም ተማሪዎች አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማሪያ መርሃ ግብር ተግባራዊ ማድረግ፥ እና

   f) በትምህርት ቤት፣ በስራ እና በማህበራዊ መቼቶች ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ የወሲባዊ ግፊቶችን የሚቀንሱ ባህሪያትን እና አመለካከቶችን ለማዳበር ተማሪዎችን ስለ ጾታዊ ብልግና እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለማስተማር እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች እድሎችን መጠቀም።

2. ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ-የምትጥስ ማንኛውም ተማሪ በ MCPS የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ መሠረት ለጥፋቱ(ቷ) ምላሽ በሚሰጥ ደረጃ ተገቢ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰዳል።

3. በማንኛውም ጊዜ Title IX በመጣስ ወሲባዊ ትንኮሳ እንደደረሰባ(በ)ት የተጠረጠረ(ች) ተማሪ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያልተገደበ፣ ለ "U.S. Department of Education's Office for Civil Rights (OCR)" ቅሬታ ማቅረብ ትችላለች/ይችላል። አንድ ተማሪ በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ቢሮ ቅሬታ

ከማቅረቡ በፊት ወይም በኋላ ለ MCPS አቤቱታ ማቅረብ አይጠበቅበ(ባ)ትም።

U.S. Department of Education, Office of Civil Rights
የዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት፣ የሲቪል መብቶች ቢሮ
OCR ኤሌክትሮኒክ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ
(http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html)፣ ወይም
U.S. Department of Education, Office for Civil Rights
Lyndon Baines Johnson Department of Education Building
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202-1100

4. በማንኛውም ጊዜ፣ ወሲባዊ ባህርይ እንዳላቸው የሚጠረጠሩ ወንጀሎችን ተማሪ ለህግ አስከባሪዎች በቀጥታ ሪፖርት ማድረግ ወይም አቤቱታ ማቅረብ ይችላል-ትችላለች፡-

Montgomery County Police Department
Special Victims Investigation Division
100 Edison Park Drive
Gaithersburg, MD 20878

ወይም ለ Safe Schools Maryland Tip Line 1-833-MD-B-SAFE

**F. ግምገማ እና ሪፖርት**

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በዚህ ፖሊሲ ድንጋጌ መሠረት ሪፖርት የተደረጉ የወሲብ ትንኮሳዎችን እና ጾታዊ ጥቃቶችን እንዲሁም ሌሎች የቀረቡ ቅሬታዎችን በየሩብ ዓመቱ ለቦርዱ ሪፖርት ያደርጋል/ታደርጋለች። የክስተቱ ሪፖርቶች ካለፈው ሩብ ዓመት ጀምሮ የተፈጸሙ ተከታታይ ክስተቶችን መረጃዎች ማካተት አለባቸው። ስነ ሥርአት ያለማክበር ሪፖርቱ ላይ ቅሬታ እና የመፍትሄ ሂደቶችን፥ ግምገማዎችን እና ማሻሻያዎችን፥ የስልጠና ስታቲስቲክስ እና የጊዜ ሰሌዳዎች፥ በሁሉም የ MCPS ትምህርት ቤቶች፣ ቢሮዎች እና የሥራ ቦታዎች ውስጥ የሥራ አከባቢዎች ቀጣይ ግምገማ እና ለዚህ ፖሊሲ ስኬታማ ትግበራ አግባብነት ያላቸው በ MCPS የታቀዱ ወይም የሚከናወኑ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች መካተት አለባቸው።

2. ይህ ፖሊሲ በቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሠረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመገማል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Title VII of the Civil Rights Act of 1964, as amended, 42 U.S.C. §2000e et seq; Title IX of the Education Amendments of 1972, 20 U.S.C. §1681 et seq; 29 C.F.R. §1604,11; 34 C.F.R 106.30(a); Annotated Code of Maryland, Education Article, §6-104, §6-113, §6-113.2, §7-303.1, §7-424, §7-424.1, §7-424.3, and §11-60; Annotated Code of Maryland, State Government Article, Title 20, Human Relations; Code of Maryland Regulations §13A.12.05.02; Student Code of Conduct in MCPS; MCPS Employee Code of Conduct; MCPS Guidelines for Student Gender Identity

**የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፡-** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 837-92፥ ኖቬምበር 23/1992፤ የተሻሻለበት የውሳኔ ቁጥር 466-96 ጁን 24/1996፤ ጁን 29/2021 በውሳኔ ቁጥር 322-21

ተሻሽሏል።